11. ፈውስን ይሰጣሉ ብሎ የተለያዩ ቁሳቁሶችን መሸጥና ሌሎች ባዕዳዊ ልምምዶችን የማይፈጽሙ መሆናቸው ሲረጋገጥ፣
12. ኑፋቄያዊ ተክለ ሰውነት የማይገነቡ ማለትም ክርስቶስን እንጂ ራሳቸውን የማይሰብኩ፣
13. በየትኛውም ደረጃ ካለ ኅብረት ማለትም የክልል፣ የዞንና የከተማ ኅብረት ጋር በሚደረግ የጀማ ስብከተ ወንጌል፣
    ሀ. የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዋና ቢሮ ሳያውቅ ማስታወቂያዎችን በኅብረቱ ስም በማንኛውም ሚዲያዎቻቸው ወይም በማንኛው ሚዲያ (ቻናሎች) የማያስተላልፉ
    ለ. ከተለመደውና ሰው በፈቃዱ ከሚሰጠው መባ ውጭ በማናቸውም መንገድ ለራሳቸውም ሆነ ፕሮግራም ለአዘጋጀው (የክልል፣ የዞን ወይም የከተማ ኅብረት) ክፍል ገንዘብ ላይሰበስቡ (fund rise) የሚስማሙ ሲሆንና ይህንንም ሲያረጋግጡ በአጋር አባልነት ይቀበላል፣
14. በእስካሁኑ የአገልግሎት ጉዟቸው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ላጠፉት ጥፋት በግልፅ ይቅርታ ለመጠየቅ የተዘጋጁ፣

## IV. የኅብረቱ ግዴታና ሃላፊነት

ኅብረቱ ለሌሎች ተባባሪ አባላት የሚያደርገው ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጋር አባልነት የሚቀበላቸው አብያተ ክርስቲያናት ለሙሉ አባልነት የሚያበቃቸው መስፈርት ላይ እስኪደርሱ ድረስ፣

1. ለተባባሪ አባላት በደንቡ መሠረት የሚደረገውን ትብብርና ድጋፍ ያደርጋል፣
2. ስልጠናዎች፣ ወርክሾፖችና ምክክሮች ያዘጋጅላቸዋል፣
3. ኅብረቱ የሚያዘጋጃቸው የተለያዩ ስልጠናዎችና ዐውደጥናቶች ላይ በተወሰነ ቁጥር በውክልና እንዲሳተፉ ያደርጋል፣
4. ለሕይወታቸውና ለአገልግሎታቸው ስምረት የሚቻለውን በጎ አስተዋጽዖ ያደርጋል፣
5. ግንኙነቱ በዚህ መግባቢያ ሰነድ መሠረት በአግባቡ እየተፈጸመ መሆኑን በጋራ በየስድስት ወሩ የሚታይና የሚገመገም ይሆናል፣

## V. የግንኙነት መቋረጥ ምክንያቶች

1. ከላይ እንደ ግዴታ የተዘረዘሩት ጉዳዮች በከፊል ወይም በሙሉ ከተጣሱ ኅብረቱ እውቅናውን ይነሳል፣ መንሳቱንም በግልፅ ያሳውቃል
2. መሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ልምምዶችና የሞራል እና የቅድስና ጉድለቶች ሲፈጸሙ ምክር መስጠት ቅድሚያ ቢሆንም ምክርና ተግሳጽ ተቀብሎ ለማስተካከል የማይፈልጉትን በይፋ እውቅና ይከለክላል ወይም እውቅናውን ያነሳል፡፡

ስለ ኅብረቱ
ቀን 18/03/2016

ስለአጋር አባል ቤተ እምነቱ
ቀን 12/03/2016

# የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት

ከኢ.ወ.አ.ክ.ኅብረት ጋር በመተባበር ማገልገል ለሚፈልጉ አብያተ ክርስቲያናትና አገልግሎቶች ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነትና ከግንኙነቱም ስለሚመነጩ ጉዳዮች የሚሆን የመግባቢያ ሰነድ፣

## I. አጭር ርዕስ

**ትርጉም፡-** አጋር አባል (Affiliate members)

በዚህ የመግባቢያ ሰነድ፣ "አጋር አባል" የሚለው መጠሪያ፣ መተዳደሪያ ደንቡ በሚፈቅደው መሠረት አብያተ ክርስቲያናቱ የኅብረቱ አባል እስኪሆኑ በሚኖረው የጊዜ ገደብ፣ ከኅብረቱ ጋር በቅርበት መንፈሳዊ ኅብረት ለማድረግ የተስማሙትን የሚመለከት ይሆናል፡፡

## II. የመግቢያ አሳብ

የመግባቢያ ሰነዱ፣ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት አዳዲስ ቤተ እምነቶችን በአባልነት ለመቀበል ያወጣውን መስፈርት ሊያሟሉ ያልቻሉ አብያተ ክርስቲያናትን በአጋር አባልነት ለመቀበል ያዘጋጀው ሰነድ ሲሆን፣ የሰነዱን ዝርዝር ነጥቦች የሚቀበል ቤተ እምነት የኅብረቱን ራዕይ፣ ዓላማ፣ ተልዕኮ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ እንዲሁም የኅብረቱ ጠቅላላ ጉባዔው በተለያዩ ወቅቶች ያሳለፋቸውን የአቋም መግለጫዎች ተቀብሎ ተግባራዊ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡

## III. የአጋር አባላቱ (Affiliate members) ግዴታና ሃላፊነት

በኅብረቱ መተዳደሪያ ደንብ ከሌሎች ተባባሪ አባላት የሚጠበቁ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣

1. የኢትዮጵያ ሕግ በሚጠይቀው መሠረት፣ በሕግ አግባብ የተመዘገቡ፣
2. በአስተምህሮ፣ በልምምድና በሞራል ወይም በቅድስና ከኅብረቱ ጋር ተመሳሳይ ወይም አንድ ዓይነት አቋም ያላቸው፣
3. የወንጌላውያንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረታዊ አስተምህሮ፣ የኅብረቱን መተዳደሪያ ደንብና የእምነት አንቀፅ የሚቀበሉ፣
4. ሥልተ አመራራቸው የአገልጋይ/ሎሌነት መርህን የሚከተልና በተግባር የሚገለፅ ሲሆን፣
5. የኅብረቱን ራዕይ፣ ዓላማና ተልዕኮ የሚቀበሉ ወይም በተፃራሪ የማይቆሙ፣
6. የኅብረቱን ምክርና እገዛ እንዲሁም የእርምት ሀሳብ የሚቀበሉ መሆናቸውን በይፋ የሚያስታውቁ፣
7. በአገልግሎታቸውም ሆነ በአመራራቸው ክርስቶስንና ወንጌሉን ማዕከላዊ አድርገው የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን በተግባር የሚያሳዩ፣
8. ከኅብረቱ መሥራች ቤተ እምነቶች ጋር መልካም ግንኙነት የሚያደርጉ፣
9. በአስተምህሮአቸው፣ በልምምዳቸውና በተግባራዊ እንቅስቃሴያቸው በኅብረቱ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸውን፣ ከርቱዕ ክርስትና አስተምህሮ ያፈነገጡ በማለት ኅብረቱ ካገለላቸው ተቋማት ጋር የተለየ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ኅብረቱ በአጋር አባልነት ይቀበላቸዋል፣
10. የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀምን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በተለይም አዲስ ኪዳናዊ መርህ የሚከተሉና በጸጋ ስጦታዎች ስም የማይነግዱ መሆናቸው ማለትም፣ የተጸለየባቸው ናቸው፣

Evangelical Churches Fellowship of Ethiopia

First Priority Student & Youth Ministry

12/03/2016

0810356511